


ይህ በራሪ ጽሁፍ የሚዘጋጅው በሰሜን አሜሪካ የአንድነት ድጋፍ ማህበር ድርጅት የህዝብ ግንኙንት ነው። ዓላማው ወቅታዊ ዘጋባዎችን ተንተርሶ ከሀገር ውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊንያን በሀገር ቤት ውስጥ የሚደረገውን ዲሞክራሲያዊ ትግል ግንዛቤ እንዲኖራቸው በማድረግና ትርጉም ያለው ድጋፍ እንዲያደርጉ ለማበረታታ ነው ።

## ዛሬም ኢትዮጵያዊነት ያሸንፋል!!

የኢትዮያ ህዝብ ለአያሌ ዘመናት በገዢዎች ቀንበር ታፍኖ የኖረ ቢሆንም አንድነቱ አልተናጋም ለውጭ ጠላትም አልተበገረም።
ሠላም ጦርነትን ሀዘንና ደስታን እንደአመጣጣቸው በጋራ እየተካፈለ ተጋብቶ ተዋልዶ በአንድነት ለብዙ ሺህ ዘመናት የኖረው የኢትዮጵያ ህዝብ ላለፉት 18 ዓመታት በወያኔ የዘር ፖለቲካ ሲታመስ ቆይቷል።

የብሄረሰቦችን እኩልነት ላስከብር፤ ዲሞክራሲን፡እውን ላደርግ መጣሁ ሲል ሲያደነቁረን የኖረው የወያኔ መንግስት እውክለዋለሁ እወደዋለሁ የሚለውን የትግራይ ህዝብ ከሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ ነጥሎ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ሊያናክሰውና ሊያቆራርጠው ያልቆፈረው ጉድጓድ አልነበረም። ይሁን እንጂ ዛሬ የመላው ብሄረሰብ ተወካዮች በተቃውሞ ጎራ ተሰልፈው በአንድነት ወያኔን ሲፋለሙት መመልከት ለኢትዮጵያውነት እያበበ መምጣት ተጨባጭ ማረጋገጫ ሆኗል።

በዲሞክራሲ ስም ዲሞክራሲን እያፈነ፤ በብሄረሰብ እኩልነት ስም ህዝብን በጎሳ እየከፋፈለና እያናከሰ፤በህግ የበላይነት ስም በተቃዋሚዎችና በደጋፊዎቻቸው ላይ የራሱን የበላይነት እያረጋገጠ በሀገር ልማት ስም የጥቂት ግለሰቦችን ኪስ እያደለበ ህዝቡን በቃላት ብቻ የሚደልለው የወያኔ መንግስት ዛሬ እርቃኑን ቀርቷል። እወክለዋለሁ በሚለው በትግራይ ህዝብ እንኳን ሳይቀር መተፋት ጀምሯል።

በቅርቡ በመቀሌ ከተማ መድረክ በጠራው ስብሰባ ላይ የተገኘው ከ5ሺህ በላይ የሚቆጠር ህዝብ ያረጋገጠው ነገር ቢኖር በኢትዮጵያ የአንድነት ታሪክ ውስጥ ሁነኛ ስፍራ ያለው የትግራይ ህዝብ ከቀሪው የኢትዮጵያ ህዝብ ሊለየው የሚችል ምንም ዓይነት ኀይል እንደሌለ ነው።አንድነት ለብሄረሰብና ለግለሰብ ነጻነት ባለው ጽኑ እምነት ከውነተኛ የህዝብ ተወካዮች ጋር ግንባር ፈጥሮ በመድረክ ውስጥ ከፍተኛ አስተዋጾ እያበረከተ ነው። መድርክ በሰላማዊ ትግል ከወያኔ ጋር የውድድር ፍልሚያ ውስጥ ሲገባ ሊያስመዘግበው የሚችለው ተጨባጭ ውጤት እንዳለ በማመን ነው።እውነተኛ ተቀዋሚዎች ሊያስመዘግቡ የሚችሉት ትልቁ ውጤት በምርጫ ማሸነፍ ብቻ ሳይሆን ህዝቡን እደትናንቱ ሁሉ ዛሬም ለቁርጠኛ ትግል ማነሳሳት እና ትግሉ በቀጣይነት እንዲቀጣጠል ማድረግ መሆኑን የተገነዘበው ወያኔ የአልሞት ባይ ተጋዳይነቱን በትር አንስቶባቸዋል።

የወያኔ መንግስትና ካድሬዎች በመላው ሀገሪቱ የአፈና መረባቸውን ዘርግተው የመድረክንና የሌሎች ተቃዋሚ ድርጅችን እጩ ተወዳዳሪዎች እያስፈራሩ፤ እያሳደዱና እየገደሉ ከምርጫው መስመር እንዲወጡ እየገፉፏቸው ነው።

ይህም ሁሉ ይሁን እንጂ ከወያኔ መንግስት የሚሰነዘርባቸውን ጥቃት ተቋቁመው የተገኘውን ቀዳዳ በመጠቀም ህዝቡን ለምርጫ ውሳኔ እያነሳሱት በመሆኑ ተጨባጭ ውጤት እንደሚያስመዘግቡ አጠያያቂ አይደለም።የትግራይን ክልል ጨምሮ በሁሉም ክልሎች እጩ ተውዳዳሪዎችን ያሰማራው መድረክ ህዝቡ ከጀርባው በመሰለፍና ድምጹንም በመስጠት ዛሬም እንደትናንቱ ዘረኝነት ሳይሆን ኢትዮጵያነት እንደሚሸንፍ በውሳኔው ያረጋግጣል።

### መድረክና እንቅስቃሲዎቹ

መድረክ ለረጅም ዘመናት ስንጠብቀው የነበረውን፤የተለያየ አመለካከት ያላቸውን ኢትዮጵያውያኖች፤ለአገሪቷ ዘላቂ መፍትሄ ሊያመጣ ይችላል በሚል በአንድ ጠረጴዛ አሰባስቦ ስለኢትዮጵያዊነት ብቻ መምከር በመጀምሩ ዛሬ በመላ ሀገሪቱ ላይ የሚደርገውን ህዝባዊ ድጋፍ ለመጎናጸፍ በቅቷል።
መድረክ በአክሱም ፤በአድዋ በመቀሌና በተንቤን ያደረገው ስብሰባ የወያኔን እጩ ተወዳዳሪዎች አስደንግጦል።

ይህ እንዳለ ሆኖ መድርክ በመላው አዲስ አበባ ባደረገው ህዝባዊ ስብሰባ በሺዎች የሚቆጠሩ የአካባቢው ተነውሪዎች በስብሰባው ላይ በመገኘት የገዢውን ማስፍራሪያ በድፍርት ሰብረውታል።

ባሳየውም አጭር የስራ ወቅትም ያደረገውን ፖለቲካዊ ድል አመስግነዋል; በትግራይ ስብሰባ ወቅት የመድርክ አባል በሆነው የኦሮሞ ፌደራልስት ንቅናቄ መሪ የሆኑት አቶ ቡልቻ ደመቅሳ የተደረገው ንግግር አብዛኛው የስብሰባ ታዳሚዎችን ያስደመመ ነበር በንግግራቸው ወቅትም ስሜቱ ያልተነካ ሰው አልነበረም።ካለፉት ስርዓቶች ጋር አነጻጽረው ኢትዮጵያዊነት ትርጉም ያለውና ወድፊትም እያበበ የሚኖር መሆንን አስጋንዝበዋል።
ህወሀት ሥልጣን ላይ ለመውጣትም ሆነ በስልጣን ላይ ለመቆየት ሲጠቀምበት የቆየው የዘር ፖለቲካ እየመከነ ለምምጣቱ ምልክቶች በጉልህ እየታዩ ነው።በመድርክ ውስጥ የተሰባሰቡትና ብዙሀኑን የኢትዮጵያ ህዝብ የሚወክሉት 8 ፓርቴዎች በአንድነት በመሆን ለውድድር የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ዋነኛ ምልክት ነው። መድረክክ እንደ ኢህድግ የማስመሰል ጥምረት ሳይሆን የህዝብ ተወካይነደታቸውን በተቃውሞ ትግል ውስጥ ያስመሰከሩ ፓርቲዎች ለኢትዮጵያዊነት የጋራ ዓላማ የተሰለፉበት ግንባር ነው። በመሆኑም ዛሬ ለኢትዮጵያ ህዝብ ምርጫ መድረክ ወይስ ህወሀት? ኢትዮጵያዊነት ወይስ ዘረኝነት?የሚል ሆኗል። የኢትዮጵያ ህዝብ ትላንት ለቅንጅት እንደሰጠው ድጋፍና ድምጽ ሁሉ ዛሬም ከመድረክ ጎን በመሰለፍ ድጋፉን በመስጠት ኢትዮጵያዊነት እንደሚይሸንፍ በውስኔው በድጋሚ ያረጋግጣል።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር !!